HEALTH
CLUSTER

አማራ እና ትግራይ ኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ በአማራ እና ትግራይ ክልሎች ውስጥ ለጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል

የትግበራ ግምገማ

ሰኔ 2025

መነሻ

የተለያዩ የሰብዓዊ ቀውሶች ለሴቶችና ለልጃገረዶች የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ከፍተኛ ስጋት የሚጋርጡ ሲሆን ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት፤ ደኅንነቱ ላልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ፤ በቂ ላልሆነ የወሊድ እንክብካቤ ፤ ለሕመም እና ለሞት ዋና መንስኤዎች ናቸው። የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ላይ ባሉት ውስን ሀብቶች ምክኒያት የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶች ይስተዋላሉ ። ። የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል (Minimum Initial Service Package)እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ማዕቀፍ የሚያቀርብ ሲሆን በሰብዓዊ ድጋፍ ተግባራት ውስጥ በአሁኑ ጊዘ እንደ አንድ መስፈርት ሆኗል። በኢትዮጵያ በአማራ እና በትግራይ ክልሎች የተደረገው ይህ መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ሂደት ግምገማ ዓላማው የትግበራ ሂደቱን ለመገምገም ሲሆን የአገልግሎቱን ተደራሽነት፣ ጥራት፣ እንቅፋቶች፣ አስቻይ ሁኔታዎች እና የቁልፍ ተዋናዮች ተሳትፎን በመገምገም ላይ ያተኩራል፤ በተጨማሪም ለአገልግሎቱ እየቀረበ ያለውን የገንዘብ ድጋፍ እና የኮቪድ-19 ተጽዕኖዎችን ይመረምራል።

ዓውድ

ቁልፍ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰነዶች ማለትም—የጤና ፖሊሲ፣ የጤና ሴክተር የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ፣ ብሔራዊ የወጣቶች የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ስትራቴጂክ እቅዶች—መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅልን አስፈላጊነት ያጎላሉ። እነዚህ ሰነዶች አስፈላጊውን የድንገተኛ ጊዘ የጤና አገልግሎት ምላሽ መስጠትን፤ የሪፈራል ሥርዓትን ማጠናከር ፤ ለወጣቶች ተደራሽነት ቅድሚያ መስጠትን እንዲሁም ያልተሟላ የአገልግሎት ሽፋን ባላቸው አካባቢዎች ራሰ አገዝ የጤና ክብካቤ ማበረታታት ላይ ትኩረት ይሰጣሉ ።

ሆኖም ግን እነዚህ ደጋፊ ፖሊሲዎች ቢኖሩም ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት እና የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ስጋቶች አሉ ። ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ሪፖርት የመደረግ መጠን ዝቅተኛ መሆን ያልተቀናጀ የድንገተኛ ጊዜ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ምላሽ ፤ በቂ የገንዘብ ድጋፍ አለመኖር ፣ ከፍተኛ የሆነ ያልታቀደ እና በወጣትነት የሚከሰት እርግዝና (በተለይም በገጠር አካባቢዎች)፡ ደኅንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት ባለመኖሩ የተነሣ የሚፈጸም ፅንስ ማቋረጥ፣ ከፍተኛ የአባለዘር በሽታዎች ፤ የኤችአይቪ ሥርጭት እንዲሁም በቅርብ አጋር የሚፈጸም ጥቃት የሥነ ተዋልዶ ጤና ውጤቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

እ.ኤ.አ ከሰኔ 2024 ጀምሮ ኢትዮጵያ 4.5 ሚሊዮን የውስጥ ተፈናቃዮች እና 933,035 ስደተኞችን አስተናግዳለች። ይህ በዋናነት በግጭት፣ በድርቅ፣ በጎሳ ግጭቶች እና በከፍተኛ የአየር ንብረት ክስተቶች ምክንያት የመጣ ነው።[2] በአማራ ክልል ብቻ ወደ 388,715 የሚገመቱ ግለሰቦች የተፈናቀሉ ሲሆን ወደመጡበት ቦታ የተመለሱ ሰዎች ቁጥር 1,386,272 ገደማ ነው።[3] በትግራይ ክልል ወደ 950,000 የሚገመቱ የውስጥ ተፈናዮች የነበሩ ሲሆን 989,704 የሚሆኑት በመመለስ ላይ ያሉ የውስጥ ተፈናዮች ናቸው።[4] በቅርቡ የተከሰቱት ጎርፍ እና በተለይም በትግራይ እና በአማራ ያለው ግጭት የተፈናቀሉ ሰዎችን ቁጥር እና የሰብዓዊ ፍላጎቶችን አባብሷል።[5,6] በዚህ የድንገተኛ ምላሽ ሂደት ላይ ለመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ትግበራን ጨምሮ አስፈላጊ ለሆኑ የሰብዓዊ ድጋፍ ጥረቶች ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት አጋጥሟል ። ችዋል። የ2024 የሰብዓዊ ድጋፍ ምላሽ ዕቅድ የ3.237 ቢሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ ቢጠይቅም ይህንን ለመሙላት ለጤና ምላሽ የሚያስፈልግ የ47.2 ሚሊዮን ዶላር ጉድለት ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ የበጀት እጥረት አጋጥማል።

የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ፍላጎቶች በኢትዮጵያ በጤና ክላስተር ሪፖርቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ይጠቀሳሉ፤ በተለይም አንድ ጥናት እንዳመለከተው እ.ኤ.አ በ2020 እና በ2021 መካከል ትግራይ ውስጥ ከ10-40% የሚሆኑት ሴቶች በሆነ መልኩ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት አጋጥሟቸዋል፣ ሁኔታውም በ2024 እየተባባሰ ሄዷል። በአማራ ክልል ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ክስተቶች የጨመሩ ሲሆን ለተጎጂዎችም ደኅንነታቸው የተጠበቀ መጠለያዎች እና የአንድ ማዕከል አገልግሎት እጥረት ተስተውሏል።[7,8] ምንም እንኳን የወሊድ መጠን ከፍ ያለ ቢሆንም በተለይም ያልተሟሉ የቤተሰብ ምጣኔ ፍላጎቶች ከፍተኛ በሆኑበት ትግራይ ውስጥ የአገልግሎት አጠቃቀሙ አሁንም ዝቅተኛ ነው።

ዘዴ

ይህ የቅይጥ-ዘዴ ጥናት በኢትዮጵያ በአማራ እና በትግራይ ክልሎች በቅርብ ጊዜ በተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ትግበራን ለመገምገም የተካሄደ ነው። መረጃ ስብሰባ የተካሄደው እ.ኤ.አ በታኅሣሥ 2024 እና በጥር 2025 መካከል ሲሆን መረጃው የተገኘው ከቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች እንዲሁም ከማኅበረሰብ አባላት እና ከውስጥ ተፈናቃዮች ጋር ከተደረጉ የቡድን ውይይቶች ነው። ጥናቱ በድምሩ ስድስት የጤና ተቋማትን፣ 12 የጤና ባለሙያዎችን ፣ ስምንት ቁልፍ መረጃ ሰጪዎችን እና 77 የማኅበረሰብ አባላትን አካቷል። በተጨማሪም መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ትግበራን፣ የአገልግሎት ጥራትን እና ያጋጠሙ ችግሮችን ገምግሟል። የመረጃ ትንተና የተከናወነው ገላጭ ስታትስቲክስን (Descriptive Statistics) ኤስፒኤኤስ (SPSS) እና ኤክሴል (Excel) በመጠቀም ሲሆን ለጥራታዊ መረጃ (Qualitative Study))ደግሞ ዲዱዝ(Dedoose) ጥቅም ላይ ውሏል። የጥናት ፈቃድ ከኢትዮጵያ ጤና አጠባበቅ ማኅበር እና ከዓለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ (አይአርሲ) የምርምር ሥነ ምግባር ኮሚተ ተገኝቷል።

ግኝቶች

መሠረተ ልማት እና የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ትግበራ ግንዛቤ

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በትግራይ እና አማራ ክልሎች ውስጥ በመሠረተ ልማት ላይ የታዩት ተግዳሮቶ እና የባለሙያዎች መፈናቀል በጤና አገልግሎት አቅርቦት ላይ ተጽዕኖ አሳድረዋል ። ትግራይ ውስጥ ብዙ ተቋማት ተዘርፈዋል ወይም ተጎድተዋል፤ ይህም 13% የሚሆኑ ተቋማት ብቻ ሥራ ላይ እንዲቆዩ አድርጓል።[9] በአማራ ከ50% በላይ የሚሆኑ የጤና ተቋማት ተጎድተዋል፤ ይህም አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ላይ ከመጠን በላይ የሆነ የታካሚዎች ቁጥር እንዲኖር አድርጓል።[10] አሁንም ቀጥለው ያሉ ግጭቶች የጤና ሥርዓቱ ላይ የበለጠ ጫና የፈጠሩ ሲሆን አንዳንድ ሪፖርቶች የጤና ባለሙያዎች ዒላማ መደረጋቸውን እና ተቋማት መዘረፋቸውን አሳይተዋል።[1]

በጤና ተቋማት በተሰራው ጥናት መሰረት በትግራይ የሚገኝ አንድየዲስትሪክት ሆስፒታል ወደ 2 ሚሊዮን ለሚጠጋ ሕዝብ የሚያገለግል ሲሆን እያንዳንዱ ጤና ጣቢያ ደግሞ ለ32,540 ሰዎች ያህል አገልግሎት ይሰጣል። የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያሳዩት ከጤና ጣቢያዎች ውስጥ 40% የሚሆኑት ብቻ የተስተካከለ የኤሌክትሪክ አቅርቦት የነበራቸው ሲሆን 60% የሚሆኑት ብቻ የሚሠራ የውሃ አቅርቦት ነበራቸው። ዋና የሪፈራል ተቋም የሆነው ሱሁል ሽረ ሆስፒታል የ24 ሰዓት የኤሌክትሪክ እና የውሃ አቅርቦት አልነበረውም። ሆኖም ግን ሁሉም ተቋማት የተለያየ ጾታ ያላቸው የሠራተኞች ስብጥርን ነበራቸው እንዲሁም ቢያንስ አንድ ብቃት ያለው ባለሙያ በየቀኑ ይገኝ ነበር።

የጥራታዊ መረጃ (Qualitative data) ግኝቶች እንደሚያሳዩት በተለያየ የጤና አገልግሎት መዋቅር ላይ ያሉ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ላይ ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ ነበር። በጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና የተክኒክ ሥራ ቡድን ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ላይ ያሉ ስድስት ዋና ዋና ዓላማዎች በተመለከተ ጠንካራ ግንዛቤ እንዳላቸው የተስተዋለ ሲሆን ይህም በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ተሳትፎ፣ በኦንላይን ሥልጠና እና በአካል በሚደረጉ ስብሰባዎች አማካኝነት የተገኙ ናቸው። በሌላ በኩል የክልል ባለድርሻ አካላት ውስን የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ሥልጠና እንደነበራቸው አሳውቀዋል። ብዙዎቹ መሠረታዊ ግንዛቤ ቢኖራቸውም ስድስቱን ዓላማዎች በግልጽ መናገር የሚችሉ ጥቂቶች ነበሩ። የሥልጠና ክፍተቶች በተለይ እንደ ቤተሰብ እቅድ እና መሠረታዊ የአስቸኳይ ጊዜ የወሊድ እና የጨቅላ ሕፃናት ሕክምና ባሉ ጉዳዮች ላይ ጎልተው ታይተዋል።አሁንም ቀጥለው ባሉ ግጭቶች ምክኒያት የሚታየው የጸጥታ እጦት እንዲሁም የገንዘብ እጥረት በክልል ደረጃ የሚሰጡ የአቅም ግንባታ ጥረቶች ላይ ትልቅ እንቅፋቶች ፈጥረዋል ።

66.7%
(4/6) የሚሆኑት የጤና ተቋማት በጾታ የተለዩ፤ የውጭ መብራት ያላቸው መጸዳጃ ቤቶች አሏቸው።

83.3%
የሚሆኑት ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ስጋትን ለመቀነስ ከውስጥ የሚቆለፉ መጸዳጃ ቤቶች አሏቸው

50
የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎች (CMR) ላይ በአገር አቀፍ ደረጃ ሥልጠና ወስደዋል።

184
የጾታዊ ጥቃት ድርጊቶች ዳሰሳ በተደረገባቸው በአራት የጤና ተቋማት (1 በትግራይ እና 3 በአማራ) በ3 ወራት ውስጥ ተዘግበዋል።

<50%
በመቶ የሚሆኑት ሰለባዎች የድህረ-ተጋላጭነት ሕክምና እና ሌሎች ጊዜ የማይሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት በ72 ሰዓታት ወሰኝ ጊዜ ውስጥ ወደ ጤና ተቋም ቀርበዋል።

የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ዓላማ 1፦

ቅንጅት እና አመራር

የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ትግበራ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ምላሾችን ለማስተባበር የተመደበ መሪ ኤጀንሲ ይፈልጋል። ከሰነዶች እንዲሁም ከቁልፍ መረጃ ሰጪዎች በተገኘው ግኝት መሰረት ኢትዮጵያ ውስጥ በብሔራዊ ደረጃ አመራር የሚሰጠው በጤና ሚኒስቴር በኩል በኢትዮጵያ ማህብረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አማካኝነት ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ፈንድ (ዩኤንኤፍፒኤ) ምክትል ሰብሳቢ ሆኖ ያገለግላል። በክልል ደረጃ ያለው ቅንጅት ደግሞ በየአካባቢው ካለው የፖለቲካ እና የደኅንነት ሁኔታ ጋር የተሳሰረ ነው። በትግራይ ክልል የነበረው ግጭት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረበት ወቅት የቅንጅታዊ ስራውን በማስተባበር የመሪነት ድርሻ የነበረው የተባበሩት መንግሥታት የሕዝብ ፈንድ (ዩኤንኤፍፒኤ) ነበር ። ከግጭቱ በሁዋላ ቀድመው በክልሉ ጤና ቢሮ ስር የነበሩ የቅንጅት መዋቅሮችን መልሶ የማዋቀር ስራ የተሰራ ሲሆን እንደ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ ሪፖርት መሰረት በአሁኑ ሰአት የክልሉ ጤና ቢሮ የትኩረት አቅጣጫ በጤና ተቋማት የሚሰጠውን የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎትን ጥራት ማሻሻል እና ከመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ወደ መደበኛ እና ሁሉን ያካተተ የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት መሸጋገር ነው ።

በአማራ ክልል በታጣቂ ቡድኖች እና በፌደራል መንግሥቱ መካከል አሁንም እየቀጠለ ባለው ግጭት ምክኒያት በመንግሥት የሚመሩ ቅንጅታዊ አሰራሮችበአብዛኛው በስራ ላይ እየዋሉ አይደለም ፡ ፡ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ውስጥ ያሉ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና የቅንጅት ጥረቶች በተበታተነ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን በዋናነት እንደ ዩኤስኤአይዲ ባሉ አጋር አካላት እና በአጋር ድርጅቶች አስተባባሪ ግብረ ኃይልን (Implementing Partners Coordination Task Force) በሚመሠረቱ መድረኮች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፤ ። (እ.ኤ.አ ጥር 2025 በተጠናቀቀው መረጃ መሠረት)።

የቅንጅት ጥረቶች ትግራይ ውስጥ ይበልጥ ጠንካራ ሆነው የሚታዩ ይመስላሉ። የክልል መንግሥቱ እና የሰብዓዊ ድጋፍ አጋር አካላት ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል። ትግራይ ውስጥ የነበረው የክልሉ ምላሽ ጤና ሚኒስቴር በብሔራዊ ደረጃ ካደረጋቸው ጥረቶች ጋር ሲነጻጸር ይበልጥ ጠንካራ የሆነ አመራር እና ቅንጅት ታይቶበታል። የግምገማ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ትግራይ ከአፋር እና ከአማራ ክልሎች የበለጠ ያልተቆራረጠትኩረት እና ድጋፍ አግኝቷል፤ ይህም በክልሎች መካከል ያለውን የሰብዓዊ ድጋፍ ምላሽ ልዩነቶችን ያሳያል። በተጨማሪም ግኝቶቻችን በጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና፣ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት እና በኤችአይቪ ንዑስ የሥራ ቡድኖች መካከል ደካማ እና የተበታተነ ቅንጅት መኖሩን ያሳዩ ሲሆን በእነዚህ የሥራ ቡድኖች እና በንዑስ ክፍሎች መካከል የነበረው ቅንጅትም አናሳ እና ያልተስተካከለ ነበር። ይህ ደግሞ በአገልግሎቶች ውሕደት እና ሀብትን በአግባቡ መጠቀም (optimization_) ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል።

ሴቶች ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ላይ ያላቸው ስጋት

- ብዙውን ጊዜ በአደገኛ አካባቢዎች ማለፍን የሚጠይቅ ወደ ጤና ተቋማት ለመድረስ የሚደረግ ረጅም ጉዞ።
- የውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው ካምፖች ውስጥ ያሉ ደኅንነታቸው ያልተጠበቀ የመጠለያ ሁኔታዎች፣ ብዙውን ጊዜ ምንም ዓይነት እውነተኛ ጥበቃ ወይም ግላዊነት የማይሰጡ በቀላሉ በሚሰበሩ የላስቲክ ቁሶች የሚሠሩ ናቸው።
- በማኅበረሰቡም ሆነ በሰብዓዊ ምላሽ ሰጪዎች በቅርብ አጋር የሚፈጸም ጥቃትን ችላ መባሉ።
- ደኅንነቱ ያልተጠበቀ የትምህርት ቤት ጉዞ እና የትራንስፖርት እጥረት በተለይ ለታዳጊ ልጃገረዶች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።
- የተጨናነቁ የመኖሪያ ሁኔታዎች በተለይ እንደ መጸዳጃ ቤቶች ያሉ የጋራ መገልገያዎች አጠገብ ለጥቃት የመጋለጥ አደጋን ይጨምራሉ።

የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ዓላማ 2፡-

ጾታዊ ጥቃቶችን መከላከል እና በሚከሰቱበት ጊዜም በተጎጂዎች ላይ ለሚያመጡት ጉዳቶች አሰፈላጊውን ህክምና መስጠት

በአማራ እና ትግራይ ክልሎች ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የተለያዩ ሰብአዊ ቀውሶች በሚታይበቸው አካባቢዎች ውስጥ ሆነው በሚኖሩ ማኅበረሰቦች ውስጥ አሁንም በሰፊው ይስተዋላል። ዳሰሳ በተደረገባቸው በሁሉም ተቋማት ውስጥ በተለያየ ደረጃ አደጋ ላለባቸው ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ሰለባዎች የሕክምና እንክብካቤ ተሰጥቷል። ይህም የድህረ ተጋላጭነት ሕክምና፣ የድንገተኛ እርግዝና መከላከያ፣ ለአባለዘር በሽታዎች የሚሰጥ አንቲባዮቲክስ፣ የእርግዝና ምርመራ እና በሕግ በሚፈቀደው መጠን ደኅንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ እንክብካቤ ማድረግ ያካትታል ። በተጨማሪም ደኅንነቱ የተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ ተጨማሪ እንክብካቤ ለማግኘት እና የማኅበረ ሥነ-ልቦናዊ እና የሕግ ድጋፍ ለማግኘት ሪፈር ማድረግን ያካትታል።

ማኅበረሰቡ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን እና ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ያለውን ግንዛቤ ለማሻሻል ጥረቶች የተደረጉ ሲሆን ከእነዚህ ጥረቶች መካከል የተወሰኑት በአዋላጅ ባለሙያች የሚመሩ የማኅበረሰብ ውይይቶች፣ ከተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች (ለምሳሌ የሃይማኖት መሪዎች፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የወረዳ ባለሥልጣናት) ጋር የተደረጉ የሕዝብ ውይይቶች እና ለነፍሰ ጡር ሴቶች የተዘጋጁ ጉባኤዎች ይገኙበታል። ነገር ግን ማኅበረሰቡ ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን እንዲሁም የመገለል ፍራቻ ተጎጂዎችን እንክብካቤን ከመፈለግ በእጅጉ አግዷቸዋል። በተለይ በልጃገረዶች ዘንድ ያለው የመገፋት፣ የማኅበራዊ መገለል እና የኃብቻ እድል ፍርሃት ተጎጂዎች ሁኔታቸውን እንዳይገልጹ አድርጓል። በተጨማሪም ተቋማት የታካሚዎቻቸውን ግላዊ መረጃ በአግባቡ ከመያዝ አንጻር ጉድለት የታየባቸው ሲሆን የውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው ካምፖች ውስጥ ደኅንነታቸው ያልተጠበቀ ሁኔታዎች፣ በቂ ያልሆኑ መጠለያዎች እና ደኅነታቸውን ያልጠበቁ መጸዳጃ ቤቶች መኖራቸው የአደጋ ተጋላጭነትን ከፍ ያደርጋል ፡፡

በተጨማሪም በተለይም በቅርብ አጋር የሚፈጸም ጥቃት በተመለከተ በማኅበረሰብ ደረጃ ያለው ንቅናቄ ውስን ነው። የትግራይ ክልል ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደገለጹት ከግጭት ጋር ተያያዥነት ያለው ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ይበልጥ አሰቃቂ እንደሆነ ስለሚታሰብ ተጨማሪ ትኩረት ይሰጠዋል። ይህ ደግሞ በቅርብ አጋር የሚፈጸም ጥቃት እና የቤት ውስጥ ጥቃት ችላ እንዲባል ወይም ተገቢው ምላሽ ሳይሰጠው እንዲለመድ አድርጓል። በአጠቃላይ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች በሁለቱም ክልሎች ውስጥ አስገድዶ መድፈር በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ሪፖርት እንደሚደረግ አጽንዖት ሰጥተዋል ፡፡

በቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ገለጻ መሠረት አማራ ክልል ውስጥ ያለው ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት ሥራ በጥሩ ሁኔታ የተቀናጀ አይደለም፤ የሀብት አቅርቦት ውስንነትም አለ። በተቃራኒው ትግራይ ውስጥ እንዲህ ያሉ ጥረቶች በአንጻራዊነት በጥሩ ሁነታ እየተሰሩ ሲሆን ከሌሎች የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ጋር ሲወዳደር ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን የመከላከል እና ምላሽ የመስጠት ጥረቶች በአንጻራዊነት ጠንካራ ናቸው። እነዚህ ጥረቶች የክልሉ መንግሥት የወሰዳቸውን የሚከተሉትን እርምጃዎች ያካትታሉ፦ ለእያንዳንዱ ተቋም ቢያንስ ሁለት የጤና ባለሙያዎችን በጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና ክሊኒካዊ አያያዝ ላይ ስልጠና መስጠት እንዲሁም የብሔራዊ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት አያያዝ መመሪያዎችን ወደ ትግርኛ መተርጎም እና ማሠራጨት ይገኙበታል ፡፡ ይህ የመመሪያ ትርጉም በዓለም ጤና ድርጅት፣ በዩኤንኤፍፒኤ እና በሲኤስቲ ድጋፍ የተከናወነ ነው ፡፡

የጥናቱግኝቶች እንደሚያሳዩት በሁለቱ ክልሎች ባሉ በርካታ ከተሞች ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ተጎጂዎች ድጋፍ ለመስጠት ደኅንነታቸው የተጠበቀ መጠለያዎች ተቋቁመዋል። ሆኖም ግን የአስቸኳይ ጊዜ የገንዘብ ድጋፍ በፕሮጀክቶች መቋረጥ ምክንያት በተደጋጋሚ ይቆማል። በተጨማሪም በማገገም ሂደት ውስጥ ፈተና ሆኖ የሚቀጥለው የባለድርሻ አካላት ድጋፍ በማግኘት ሂደት ውስጥ የተጎጂዎችን ምሥጢራዊነት ጠብቆ ማቆየት ነው።

27.3%

የ SRH አቅራቢዎች ያምናሉ የሞራል ፍርዶችን በመጥቀስ "PrEP (ቅድመ-መጋለጥ ፕሮፊሊሲስ) ከተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት እና ከጾታ ግንኙነት ሰራተኞች መከልከል አለበት."

33.3%

የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች የአለም ጤና ድርጅት መመሪያ ከሚያስቀምጠው በተቃራኒ «ኤችአይቪ ያለባቸው እናቶች የፀረ ኤችአይቪ መድሃኒት እየወሰዱ ቢሆንም እንኳ አዲስ ለተወለዱ ሕፃናት ጡት ማጥባት የለባቸውም» ብለው ያምናሉ።

ኤችአይቪን/የአባለዘር በሽታዎችን መከላከል እና አገልግሎቶች ላይ ተጨማሪ ክፍተቶች

- አማራ ክልል ከሚገኙት ሦስት የጤና ተቋማት ውስጥ አንዱ ብቻ ለቋሚ ተጠቃሚዎች የኤችአይቪ ሕክምና ፕሮቶኮሎች አሉት።
- ከስድስት የጤና ተቋማት ውስጥ አንዱ ብቻ የሄፐታይተስ ቢ ክትባት እና የሄፐታይተስ ቢ የበሽታ መከላከያ ግሎቡሊን ይሰጣሉ።
- የኤችአይቪ መመርመሪያ መሣሪያዎች እጥረት፣ የአባለዘር በሽታዎች ምርመራዎች አለመኖር፣ የኤችአይቪ ህክምና አገልግሎት ከሌሎች የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ጋር አለመቀናጀት።
- ስለ አባለዘር በሽታዎች ሥርጭት በቂ መረጃ አለመኖር
- የውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙ ክሊኒኮች ብቃት ያላቸው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች አለመኖር እና ከኤችአይቪ ጋር በሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ማኅበረሰባዊ መገለል።

የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ዓላማ 3፡-

የኤችአይቪ እና የአባለዘር በሽታ ሥርጭትን መከላከል

ዳሰሳ የተደረገባቸው ሁሉም ተቋማት ለአባለዘር በሽታዎች ህክምና ይሰጣሉ፣ ኤችአይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎቶች እና ኤችአይቪ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ የማህበረሰብ ክፍሎች የፀረ ኤችአይቪ መድኃኒት ይሰጣሉ። በተጨማሪም በሽታ መከላከል እና የኮንዶም ሥርጭትን በሚመለከት ፕሮቶኮሎች ተቀምጠዋል። ከጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና የዳሰሳ ጥናት በተገኘው መረጃ መሠረት ዳሰሳ ከተደረገባቸው አሥራ ሁለቱ የጤና ባለሙያዎች ውስጥ ስድስቱ በጾታዊ ጥቃት ወይም በሥራ ቦታ መጋለጥ ምክንያት የሚከሰት ኤችአይቪን ለመከላከል የድህረ ተጋላጭነት ሕክምና ሥልጠና ወይም መመሪያ አግኝተዋል። ይህ ተመሳሳይ የባለሙያዎች ቁጥር ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ከጾታዊ ጥቃት ወይም ከሥራ ተጋላጭነት በኋላ የሚከሰት ኤችአይቪን ለመከላከል የድህረ ተጋላጭነት ሕክምና አገልግሎቶችን ሰጥቷል።

ጥራታዊ ቃለመጠይቆች (Qualitative Interviews) እንደሚያሳዩት በተለይ ትግራይ ውስጥ ማኅበረሰቡ ስለ ኤችአይቪ/የአባለዘር በሽታዎች ያለው ግንዛቤ በአንጻራዊነት ጠንካራ ነበር። ትግራይ ውስጥ እንደ የኮንዶም አጠቃቀም እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ልምዶች ያሉ የመከላከያ ዘዴዎች ይታወቃሉ። ሆኖም ግን በወሲብ ሥራ የሚተዳደሩ ግለሰቦች ወይም አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች ለመሳሰሉ ቁልፍ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚደረግ የግንዛቤ ማስጨበጥ እንቅስቃሴ አልነበረም ማለት ይቻላል። የማኅበረሰብ አባላት የኤችአይቪ/ኤድስ ግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች መዳከማቸውን አጉልተው አሳይተዋል። ብዙ የወሲብ አጋሮች ያሏቸው ሴቶች እና በወሲብ ሥራ የሚተዳደሩ ግለሰቦች የታለመ ትምህርት ወይም የመከላከያ ግብዓቶችን አያገኙም። ከኤችአይቪ ጋር በሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚደረግ መገለልም ማኅበረሰቡ ውስጥ በጣም የተለመደ ነው። ይህም ተጨማሪ የማኅበረሰብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አስፈላጊነትን ያሳያል።

የኤችአይቪ የምላሽ ጥረቶችም እንዲሁ የተገደቡ ነበሩ። ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እና የማኅበረሰብ አባላት እንደገለጹት የመሣሪያዎች ማለቅ እና በቂ ያልሆኑ የላብራቶሪ ምርመራ መሣሪያዎች መኖር ውጤታማ የሆነ የኤችአይቪ ምላሽ እንዳይኖር አድርገዋል ይህ በተለይ የምርመራ መሣሪያዎች እና ብቃት ያላቸው ሠራተኞች በሌሉባቸው የውስጥ ተፈናቃዮች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ይታያል።የኤችአይቪ ህክምና ከአጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ጋር ሁል ጊዜ የተቀናጀ ስላልነበር   ተገልጋዮች ብዙውን ጊዜ ሕክምናውን ለማግኘት መጓዝ ወይም ወደ ውጭ ሪፈር ለመደረግ ይገደዳሉ።

የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ዓላማ 4፡-

የእናቶች እና የጨቅላ ሕፃናት ሕመም እና ሞትን መከላከል

በጥናቱ በተካተቱት ክልሎች ውስጥ የእናቶች እና የጨቅላ ሕፃናት የጤና ሁነታ አሳሳቢ ሆኖ ቀጥለዋል። በግጭት ጊዜያት ወቅት የጨቅላ ሕፃናት ሞት መጨመሩ ሪፖርት ተደርጓል። ትግራይ ውስጥ የጨቅላ ሕፃናት ሞት እ.ኤ.አ በ2020 እና በ2022 መካከል ከግጭቱ በፊት ከነበረው ጊዜ (እ.ኤ.አ 2019)[11] ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል። በተመሳሳይ በአማራ ክልል ከፍተኛ መጠን ያለው ማስቀረት የሚቻል የጨቅላ ሕፃናት ሞት ታይቶ ነበር።[12]

በተቋማቱ ውስጥ የተደረጉት የዳሰሳ ጥናቶች   እንዳመለከቱት ምንም እንኳን በተቃኙት ሁሉም ቦታዎች ላይ መደበኛ የማዋለድ አገልግሎቶች ቢኖሩም አጠቃላይ ድንገተኛ የእርግዝና እና የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ (CEmONC) ሲሰጥ የነበረው ሱሁል ሽረ ሆስፒታል ብቻ ነበር ።   ይህ ሆስፒታል እንደ አጠቃላይ ድንገተኛ የእርግዝና እና የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ (CEmONC) የአገልግሎት አቅርቦት ማዕከል የተደራጀ ሲሆን ለሎቹ ተቋማት መሰረታዊ ድንገተኛ የእርግዝና እና የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ (BEmONC) እንዲሰጡ የተደራጁ ናቸው ።

ከጤና ተቋማት የዳሰሳ ጥናት የተገኙ ግኝቶች እንደሚያሳዩት ለማኅበረሰቡ በተቋማት ውስጥ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ መደበኛ የማዋለድ አገልግሎት ስለመኖሩ እና ከእርግዝና ችግሮች ጋር በተያያዘ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ላይ መረጃ እንደተሰጠ ያሳያሉ። ሆኖም ግን ከሌሎች የጤና ጉዳዮች ጋር ሲነጻጸር የጤና ተቋማት ስለ አጠቃላይ እንዲሁም መሰረታዊ ድንገተኛ የእርግዝና እና የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ በተመለከተ () ያነሰ መረጃ ይሰጣሉ ።   ከዚህ በተጨማሪ በተቋማቱ የሚሰጡት የጤና

50%

ዳሰሳ ከተካኼደባቸው ከ12ቱ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አቅራቢዎች 50% የሚሆኑት የቤተሰብ ምጣኔ፣ የሕፃናት ጤና እና የእናቶች ጤና (የፅንስ ማቋረጥን ጨምሮ) መደበኛ ሥልጠና ወይም ምክር አግኝተዋል።

33.3%

የሚሆኑት የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች በመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ላይ ባለፉት 24 ወራት ውስጥ ሥልጠና አግኝተዋል።

54.5%

የሚሆኑት የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ድጋፍ ለሚደረግላት በማሕፀን ማዋለድ የቫኩም ኤክስትራክተር አጠቃቀም፣ ቦርሳ እና ጭንብል በመጠቀም ጨቅላ ሕፃናትን እስትንፋስ መስጠት እና የጨቅላ ሕፃናትን ኢንፌክሽን መቆጣጠር ላይ ሥልጠና አግኝተዋል።

54.5%

የሚሆኑት አገልግሎት ሰጪዎች ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ የማዋለድ አገልግሎት ሰጥተዋል።

ትምህርቶች ስለ መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል እና የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች በተመለከተ ለማኅበረሰቡ ለማሳወቅ እጅግ ባነሰ ሁኔታ ጥቅም ላይ ውለዋል ፡፡

ዳሰሳ የተደረገባቸው ስድስቱ የጤና ተቋማት በሙሉ የተለያዩ የድህረ ፅንስ ማቋረጥ እንክብካቤ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። ይህ ምክር መስጠትን፣ ከፅንስ ማቋረጥ በኋላ የሚደረግ የቤተሰብ ምጣኔን፣ የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን እና ሌሎች አጠቃላይ የጤና አገልግሎቶችን ያካትታል። ለድህረ ፅንስ ማቋረጥ እንክብካቤ እጅግ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉት ዘዴዎች በሕክምና እና በኤሌክትሪክ/ማኑዋል ቫኩም አስፕሬሽን ናቸው።

የሪፈራል ሥርዓት ትልቅ ችግር ነበር ፡፡ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ተቋማት ብቻ ነበሩ የሚሠራ የመጓጓዣ ሥርዓት ነበራቸው። ከስድስቱ የጤና ተቋማት አምስቱ ለድንገተኛ ጊዜ ሪፈራል ነጻ መጓጓዣ ሲሰጡ አንደኛው ደግሞ ተገልጋዮች በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይጠይቃል። ብዙ አምቡላንሶች በነዳጅ እጥረት ወይም በጥገና ችግሮች ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ ነበሩ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቤተሰቦች የራሳቸውን መጓጓዣ ማዘጋጀት እና መክፈል ነበረባቸው። አንዳንዴም በእንጨት የሚሰሩ ቃሬዛዎችን ወይም መደበኛ ያልሆኑ ተሽከርካሪዎችን ይጠቀሙ ነበር።

በትኩረት ቡድን ውይይት የተካፈሉ ሴቶች እና ልጃገረዶች በቂ ባልሆነ ወይም ባልተሟላ አምቡላንስ አቅርቦት ምክንያት፣ እናት ደም እየፈሰሳት ቢሆንም እንኳን አገልግሎት ሰጪዎች በሪፈራል ጊዜ አብረው ባለመሄዳቸው እና የክትትል አገልግሎቶች ባለመኖራቸው ምክንያት የተለያዩ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤዎች መዘግየት መኖሩን በዚህም ምክኒያት የእናቶች ጤና አደጋ ላይ መውደቁን አሳውቀዋል። ብቃት ያለው የጤና ባለሙያ ማግኘት ላይም ውስንነት የታየ ሲሆን ንጹሕ የማዋለጃ መሣሪያዎች ስርጭትም የተቆራረጠ ነበር ፡፡ ዳሰሳ ከተደረገባቸው አገልግሎት ሰጪዎች ውስጥ ባለፉት 24 ወራት ውስጥ በመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ላይ መደበኛ ሥልጠና ያገኙት ከግማሽ በታች የሚሆኑት ሲሆኑ ሥልጠናው ቁልፍ የእናቶች እና የጨቅላ ሕፃናት አገልግሎቶችን ያካትታል። በተጨማሪም ማኅበረሰቡ እነዚህ አገልግሎቶች ስለ መገኘታቸው ያለው ግንዛቤ ውስን ነበር።

ከጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች ዳሰሳ በተገኘው መረጃ መሠረት አብዛኛዎቹ አገልግሎቶች ሰጪዎች ለቅድመ ወሊድ እንክብካቤ ወደ ጤና ተቋማት ለመሄድ፣ ለሚወለዱ ሕፃናት እንክብካቤ ለማድረግ እና ወላጆች ለልጆቻቸው ጤና ያላቸውን ኃላፊነት ለመረዳት ጥሩ አመለካከት አላቸው።

ምስል 1፡-

አገልግሎት ሰጪዎች ለእናቶች እና ለጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ ያላቸው አመለካከት (N=12)



ሰንጠረዥ 1፦

ከቤተሰብ ምጣኔ/ከወሊድ መከላከያ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በትክክል የመለሱ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ሰጪዎች መቶኛ (N=12)

አገልግሎት ሰጪው የሚከተሉትን ያውቃሉ፦	Percent
ለወጣት እና ላላገቡ ሴቶች ተስማሚ የሆኑ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች	83.3
በፅንስ ማቋረጥ ችግር ምክንያት ስትታከም ለነበረች ወጣት እና ያላገባች ሴት የወሊድ መከላከያ መቼ መስጠት እንዳለባቸው	75.0
የሕክምና ባለሙያ ባልሆነ የጤና ሠራተኛ ለምሳሌ በ ማኅበረሰብ ጤና ባለሙያ ሊሰጥ የሚችል የወሊድ መከላከያ	66.7
ፕሮግራሞች እንዴት የቤተሰብ ምጣኔን የበለጠ ተቀባይነት ያለው እና ለተገልጋዮች የበለጠ ተደራሽ ማድረግ እንዳለባቸው	58.3
ከወሊድ በኋላ ከስድስት ሳምንታት በፊት ጡት ማጥባት ላይ ባለች ሴት ሊወሰዱ የሚችሉ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች	58.3
ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ እስከ 5 ቀናት ድረስ እርግዝናን ለመከላከል እንደ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ሊያገለግሉ የሚችሉ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች	41.7

ምስል 2፦

አገልግሎት ሰጪዎች ለቤተሰብ ዕቅድ እና የእርግዝና መከላከያ ያላቸው አመለካከት (N=12)



መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ዓላማ 5፦

ያልታሰበ እርግዝናን መከላከል

ከጤና ተቋማት የዳሰሰ ጥናት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በጥናቱ የተካተቱት የጤና ተቋማት የተለያዩ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን—የአጭር እና ረጅም ጊዜ አማራጮችን ጨምሮ—ይሰጣሉ። ስድስቱም ተቋማት በሙሉ በአፍ የሚወሰድ የወሊድ መከላከያ እንክብሎች፣ ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ፣ በማሕፀን የሚሰጥ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ፣ በመርፌ የሚሰጥ እና ኢምፕላንት እንዳላቸው አሳውቀዋል። ሆኖም ግን ከአጠቃቀም መረጃዎች እና ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር ከተደረጉ ቃለመጠይቆች በተገኘ መረጃ መሠረት ወጥነት የሌለው የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች የአገልግሎት አቅርቦት መኖሩን መረዳት ተችሏል። ምንም እንኳን በማሕፀን የሚቀመጡ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ቢኖሩም ግማሽ ያህሉ አገልግሎት ሰጪዎች ብቻ ናቸው ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ እነዚህን ዘዴዎች ለተጠቃሚዎች የሰጡት፤ እንዲሁም የማማከር አገልግሎት ጥራት የተለያየ ነበር። በሁለቱም ክልሎች ያሉ የማኅበረሰብ አባላት በተለይም የውስጥ ተፈናቃዮች በክሊኒክ ደረጃ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ውስን ወይም ምንም የማይገኝ መሆኑን ተናግረዋል። ብዙዎቹ በግል ፋርማሲዎች ወይም በውጭ ሪፈራሎች ላይ ጥገኛ ሆነዋል። ታዳጊ ልጃገረዶች ደግሞ ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ ማግኘት እንደማይችሉ ገልጸዋል።

የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ ዝቅተኛ ግንዛቤ እና አጉል እምነቶች በጤና እንክብካቤ ሰጪዎች ዘንድ ጭምር ዘልቀው ቆይቷል። እነዚህ እምነቶች አገልግሎት አሰጣጥን ሊጎዱ እና የሴቶችን የሥነ ተዋልዶ ነጻነት ሊሸረሽሩ ይችላሉ።

በተወሰነ ደረጃ አቅርቦት ቢኖርም ከትግራይ እና ከአማራ ክልሎች የመጡ ተሳታፊዎች በእርግዝና መከላከያ አገልግሎቶች ላይ የማይቋረጥ ተደራሽነት ከመኖሩ አኳያ ከፍተኛ ክፍተቶች እንዳሉ የገለጹ ሲሆን ይህ በዋናነት ቅዳሜ እና እሑድ አገልግሎቶች ባለመኖራቸው እና የቤተሰብ ምጣኔ ቁሳቁሶች በየጊዜው በማለቃቸው የተነሣ የሚከሰት ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ የእርግዝና መከላከያ ዘዴ አማራጮችን ይገድባል።

መሠረታዊ የመጀመሪያ አገልግሎት ጥቅል ዓላማ 6፦

አጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ቅንጅት

በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በትግራይ ከመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ወደ አጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና የሚደረገው ሽግግር ተጀምሯል። ከዩኤንኤፍፒኤ የተገኙ አንድ ቁልፍ መረጃ ሰጪ እንደሚሉት መንግሥት በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች ጤና አገልግሎቶችን በፍጥነት ለመመለስ ላደረገው «ማጣመር» ዘዴ ምስጋና ሊቸረው እንደሚገባ ገልጸዋል። በዚህ ዘዴ አዲስ አበባ የሚገኙ ሆስፒታሎች በአማራ ክልል ለተጎዱ ተቋማት የመልሶ ግንባታ እና የባለሙያ ድጋፍ አድርገዋል ይህ ዘዴ የሪፈራል ሆስፒታሎች የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ወደነበሩበት በመመለስ ረገድ ውጤታማ ሆኗል።

በተቀመጡ ደረጃዎች መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ወደ አጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ድንገተኛ ሁኔታ ከተከሰተ ከሦስት እስከ ስድስት ወራት ውስጥ በተቻለ ፍጥነት መካተት አለባቸው ፡ ነው። ነገር ግን በጥናቱ ግኝት መሰረት ወደ ከመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ ጋር የሚደረገው ውሕደት ወጥነት የሌለው ሆኖ ቀጥሏል። መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ለጤና ባለሙያዎች እስካሁን በቅድመ-አገልግሎት የሥልጠና ሥርዓት ትምህርት ውስጥ አልተካተተም። ቋሚ የፋይናንስ እጥረት ከመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ወደ አጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ለሚደረገው ሽግግር ትልቅ እንቅፋት ሆኗል። መሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል አገልግሎቶች ወደ ሰፊው የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አጠባበቅ ሥርዓት መግባታቸውን ለማረጋገጥ ለጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና የሥራ ቡድን/የክላስተር ሥርዓት ወቅታዊ ሽግግር እና የማገገሚያ ዕቅድ ፤ ቀጣይነት ያለው የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም በሰብዓዊ ድጋፍ እና በልማት ተዋናዮች መካከል ቅንጅት ያስፈልጋል። ለዘላቂ አገልግሎት አሰጣጥ የሠራተኞች ሥልጠና፣ የመሠረተ ልማት ጥገና እና የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና ትምህርት እንደ ቅድመ ሁኔታ ተጠቅሰዋል።

ደኅንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ማግኘት

ዳሰሳ ከተደረገባቸው ከስድስት ተቋማት ውስጥ አምስቱ (በአማራ ክልል የሚገኘው አንድ ጤና ተቋም ሳይጨምር) በብሔራዊ መመሪያዎች መሠረት ደኅንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ይሰጣሉ። ስድስቱም ከፅንስ ማቋረጥ በኋላ የሚሰጥ የእንክብካቤ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን አብዛኛዎቹ ቫኪዩም አስፐሬሽን የሚባለውን ፅንስ የማቋረጥ ዘዴን ይጠቀማሉ። ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ ደኅንነቱ ባልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ ምክንያት የተከሰተ አንድ የእናት ሞት ሪፖርት ተደርጓል።

ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እንዳመለከቱት በተለይ የአስገድዶ መድፈር ሰለባ የሆኑ ሴቶች ከግል መድኃኒት ቤቶች እርዳታ ስለሚፈልጉ ሪፖርት የሚደረገው ደኅንነቱ ያልተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ ቁጥር ዝቅተኛ ነው፤ ይህ ደግሞ የጤና ስጋቶችን ይጨምራል። በአማራ ክልል ከግጭት ጋር በተያያዘ በአስገድዶ መድፈር ምክንያት የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ፍላጎት ጨምሯል። ቀደም ሲል ያልተለመዱ የነበሩ ባህላዊ እና ደኅንነታቸው ያልተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ ዘዴዎች በግጭት ጊዜ እንደገና በመከሰታቸው ለእናቶች ሞት መጨመር ምክንያት ሆነዋል። ከዳሰሳ ጥናቱ የተገኘው መረጃ የአቅም ክፍተቶች እንዳሉ ጭምር ያሳያል፦ 50% የሚሆኑት ተቋማት ማኑዋል ቫክዩም አስፕሬሽን (MVA) እና ሚሶፕሮስቶልን ይጠቀማሉ።

በመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ትግበራ ላይ ተጨማሪ ስጋቶች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች

በአማራ እና በትግራይ ክልሎች የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች አሁንም እንደቀጠሉ ነው። የማኅበረሰብ አባላት በሰጡት መረጃ መሠረት የውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው ቦታዎች የሚገኙ ክሊኒኮች ከፍተኛ ደረጃ፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶች እና በቂ የሰው ኃይል የላቸውም። ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እንዳመለከቱት የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል አፈጻጸም ብዙውን ጊዜ ለችግሮች ምላሽ ለመስጠት ብቻ የሚደረግ ነበር። የቅድመ ዝግጅት እና የምላሽ ዕቅዶች የተጀመሩት ድንገተኛ አደጋዎች ከተከሰቱ በኋላ ብቻ ነበር። ምንም እንኳን እንደ የተሻሻለ የአደጋ ጊዜ አቅም እና የሀብት ማሰባሰብ ሥራ ያሉ የተወሰኑ አዎንታዊ ለውጦች ቢኖሩም ወደ አጠቃላይ የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች የተደረገው ሽግግር ወጥነት የለውም። ይህ በአብዛኛው ጊዜ በተራዘመ የመፈናቀል ሁነታዎች እና በድንገተኛ ጊዜ እና በልማት ተዋናዮች መካከል ያለው ቅንጅት ውስን በመሆኑ የመጣ ነው።

የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ያልተመጣጠኑ ፈተናዎች አሉባቸው። በማኅበረሰቡ አባላት አስተያየት መሠረት በአፍላ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች አሁንም በቂ አገልግሎት እያገኙ አይደለም። የውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው ጣቢያዎች የወጣቶች ማዕከላት የሉም። አካላዊ፣ ማኅበራዊ እና የአመለካከት መሰናክሎች አካል ጉዳተኞች የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን እንዳያገኙ እንቅፋት መሆናቸውን ቀጥለዋል። እንደ የቡና ሥነ ሥርዓቶች እና የማኅበረሰብ ኮሚዎች ያሉ የተሳትፎ ዘዴዎች የውስጥ ተፈናቃዮችን እና ማኅበረሰቡን ጾታዊ ጥቃት ስለ መከላከል፣ ስለ ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች፣ ስለሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች እና ስለ ሪፈራል ሥርዓቶች ለማስተማር ተዘርግተዋል።

ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ትግራይ እና አማራ ክልሎች ውስጥ የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል አፈጻጸም ቀጥለው ባሉ ግጭቶች፣ በውስን ሀብቶች እና በመሠረተ ልማት እጥረቶች ምክንያት ከፍተኛ ፈተናዎች አጋጥመውታል። መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማስቀጠል ጥረቶች ቢደረጉም ሙሉ ምላሽ ከማድረስ አኳያ አሁንም አሳሳቢ ክፍተቶች አሉ። የቅንጅት ሥራዎች በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ ወጥነት የጎደላቸው ሆነው የተስተዋሉ ሲሆን የፖለቲካ እና የጸጥታ ሁኔታዎች እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ያላቸውን ምላሽ ሰጪነት እና ዘላቂነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረዋል። በተለይም እንደ የጾታዊ ጥቃት እንክብካቤ፣ ኤችአይቪን/የአባለዘር በሽታዎችን መከላከል እና የቤተሰብ ምጣኔ ባሉ ዘርፎች ላይ ለጤና ባለሙያዎች አግባብነት ያለው ሥልጠና ባለማግኘታቸው ምክንያት አሁንም እየተሰጠ ያለው አገልግሎት በቂ አይደለም።

በጤና ተቋማት ላይ የተከሰቱ ዝርፊያ፣ ውድመት፣ አስተማማኝ ያልሆነ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን፣ የውሃ እጥረትን እና በቂ ያልሆነ የሪፈራል ሥርዓትን ጨምሮ በጤና መሠረተ ልማት ላይ ያለው ጫና የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች አቅርቦትን የበለጠ አዳክሟል ። በተለይም በግጭት ቀጠናዎች እና በውስጥ ተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያዎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ማግኘት በሎጀስቲክስ ውስንነቶች፣ በቅንጅት ማነስ፣ በማኅበረሰቡ ዝቅተኛ ግንዛቤ እና ስር በሰደዱ የማኅበራዊ መገለል እና ባህላዊ ልማዶች የተነሣ ተስተጓጉሏል። እንደ «ሆስፒታልን ማጣመር» ዘዴ እና የክልል የማስተባበሪያ መዋቅሮችን መተግበር በመሳሰሉ ጥረቶች ውስጥ አንዳንድ መሻሻሎች ቢኖሩም ወደ አጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች የተደረገው ሽግግር አዝጋሚ እና ወጥነት የሌለው ነበር።

አፋጣኝ የጤና አገልግሎት ክፍተቶችን ከመሙላት ባለፈ የረጅም ጊዜ የምላሽ እርምጃዎች የጤና አጠባበቅ ሥርዓቶችን ለማጠናከር፣ የአገልግሎት ቅንጅትን ለማሻሻል እንዲሁም እንደ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ያሉ ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ለማድረግ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። በአጠቃላይ ለጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና ፍላጎቶች ተደራሽ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት እና ተለዋዋጭ ለሆነው የሰብዓዊ እርዳታ ሁኔታ ምላሽ ሰጪነትን ለማረጋገጥ ቀጣይነት ያለው ዘርፈ ብዙ ትብብር፣ በቂ የገንዘብ ድጋፍ እና የታለሙ እርምጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

ምክረ ሐሳቦች

የሚከተሉት ምክረ ሐሳቦች የተዘጋጁት በቁልፍ መረጃ ሰጪዎች እና የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች በቀረቡ የማሻሻያ ሐሳቦች እንዲሁም ጥናት አድራጊዎቹ ከ የሰነድ ዳሰሳ እና ለዚህ ጥናት ከተደረገው ትንተና ያገኟቸውን ግኝቶች በማቀናጀት ነው። እነዚህ ምክረ ሐሳቦች ለብሔራዊ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና የተክኒክ ቡድን አባላት ቀርበው ይሁንታን አግኝተዋል። ምክረ ሐሳቦቹ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተከፋፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡

ለጤና ሚኒስቴር እና ለኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት

- አካባቢያዊሁኔታዎች ቢለወጡም እንኳን በአመራር እና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ቀጣይነትን ለማረጋገጥ፣ ለክልል/ የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና ማስተባበሪያ አካላት ግልጽ የሥራ ዝርዝር፣ መደበኛ የስብሰባ መርሐ ግብር እና ለብሔራዊ የማስተባበሪያ መድረክ በኃላፊነት ሪፖርት የሚያቀርቡበት ሥርዓት እንዲኖራቸው በማድረግ ተቋማዊ ማድረግ።
- ለጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ጠንካራ የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት እና ምላሽ ዕቅድ አዘጋጅቶ መተግበር ፤ የሠለጠነ የሰው ኃይል ፈጣን የሎጂስቲክስ አቅርቦት እና በቂ የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን ማረጋገጥ ፤ ።
- ድግግሞሽን ለመቀነስ እና በተለይም ጾታን መሠረት ላደረገ ጥቃት ሰለባ ለሆኑ እና ከኤችአይቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የተቀናጀ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና፣ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት እና የኤችአይቪ ንዑስ የሥራ ክፍሎች መካከል የጋራ ዓመታዊ ወይም የአስቸኳይ ጊዜ የሥራ ዕቅዶችን አዘጋጅቶ መተግበር።
- በሁሉም የሰብዓዊ እርዳታ ምዕራፎች ላይ ውጤታማ የመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል በተገቢው ሁነታ እንዲፈጸም በተለያዩ የሰብዐዊ ቀውሶች ውስጥ ለሚገኙ አካባቢዎች የሰለጠኑ የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አስተባባሪዎችን መመደብ እና በሎጂስቲክስ ድጋፍ ማድረግ ።

- ከተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎች እና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ችግሮች በደረሱ በ72 ሰዓታት ውስጥ የቴክኒክ አስተባባሪ ቡድኖችን (የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና፣ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት እና የኤችአይቪ ባለሙያዎችን) ለማሰማራት የሚያስችል የድንገተኛ ጊዜ ምላሽ ሞዴል መዘርጋት።
- በብሔራዊ እና በክልል ደረጃ መካከል ያሉ የሪፖርት ልዩነቶችን ለመፍታት የሚያስችል ማዕከላዊ የቁጥጥር ዘዴን መዘርጋት
- የመሠረታዊ መጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅልን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥራ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ (ለሐኪሞች፣ ነርሶች፣ አዋላጆች) ማካተት ። ይህም የድንገተኛ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች፣ የሥነ ተዋልዶ መብቶች እና ጾታ ላይ የተመሠረተ ጥቃት ላይ የንድፈ ሐሳብ እና የተግባር ሥልጠናን ይጨምራል።
- ከድንገተኛ አደጋ ምላሽ ወደ አጠቃላይ የጾታ እና የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ የመሸጋገር ሂደት ውስጥ ለመሠረታዊ የመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎት ጥቅል ዓላማዎች ዘላቂ የገንዘብ ድጋፍን ለማረጋገጥ ከአጠቃላይ የጤና በጀት ውስጥ ለጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና እና በጾታ ላይ ለተመሠረተ ጥቃት መከላከል እና ህክምና አገልግሎት በቂ በጀት መመደቡን ማረጋገጥ ።
- ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመተባበር ከእናቶች እና ጨቅላ ሕፃናት ሞት ጋር በተያያዘ የሚሰራውን ጥናት (maternal and perinatal death surveillance and response (MPDSR)) በማከናወን ለእናቶች እና ጨቅላ ሕፃናት ጤና እንክብካበ የተጠያቂነት ስርአትን ማጠናከር።
- ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በመተባበር ውጤታማ ምላሽ እና የበጀት አመዳደብ እንዲኖር የአባለዘር በሽታዎች ምርመራ እና የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓቶችን ማጠናከር።

ለለጋሾች፣ ለተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎች፣ ለፈጻሚ አጋሮች እና ለሙያ ማኅበራት

- ለማኅበረሰብ አገልግሎቶች የበለጠ ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ እንዲገኝ ወይም አሁን ካለው ተጨማሪ እንዲመደብመወትወት እና በዚህም ተጽዕኗቸውን የሚያዳክሙ የአስተዳደር ወጪዎችን መቀነስ።
- አገልግሎት በማይደርስባቸው አካባቢዎች በተለይም በአማራ ክልል ለተጎጂዎች የሚሰጠውን ሁሉን አቀፍ እንክብካቤ ተደራሽነት ለማስፋት የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ቁጥር መጨመር፤ ለአስገድዶ መድፈር ሰለባዎች ለሚደረግ የሕክምና አያያዝ ተጨማሪ የጤና ባለሙያዎችን ማሠልጠን እንዲሁም የአንድ ማዕከል የአገልግሎት ተደራሽነትን ወደ ገጠር እና ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች ማስፋት።
- ለጾታ ጥቃት ሰለባዎች የሚሆኑ የመጠለያ ቤቶችን ቁጥር በተለይም ራቅ ባሉ እና በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች ማስፋት እንዲሁም ሰለባዎች ሕይወታቸውን በአስተማማኝ አካባቢዎች እንደገና እንዲጀምሩ ለመርዳት የሚሰጡ አገልግሎቶችን—የሕክምና እንክብካቤ፣ የሕግ ድጋፍ፣ የሙያ ሥልጠና እና የመልሶ ማቋቋም ድጋፍን—ማጠናከር።
- በሠለጠነ ባለሙያ ስለሚደረግ የወሊድ አገልግሎት፣ ከወሊድ በኋላ ስለሚደረግ እንክብካቤ፣ ስለ ጨቅላ ሕፃናት የጤና አደጋ ምልክቶች እና ስለሚገኙ አገልግሎቶች በታለመ የማኅበረሰብ ተሳትፎ እና ከባህል ጋር በሚስማሙ የጤና ትምህርት ዘመቻዎች የእናት እና የጨቅላ ሕፃናት ጤናን ማሳደግ።
- ድንገተኛ የወሊድ እና የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ፣ ከወሊድ በኋላ ስለሚሰጥ የቤተሰብ ምጣኔ፣ ደኅንነቱ ለተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ የሚሰጥ እንክብካቤ እና ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ማካሄድ፤ በአፍላ ዕድሜ ላይ ለሚገኙ እና ላላገቡ ሴቶች ሁሉን ያካተተ እንክብካቤ መስጠት እንዲሁም ለጤና ተቀማት ድጋፋዊ ክትትሎችን ማድረግ ።
- ሁሉን አቀፍ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶችን ለረጅም ጊዜ እና የድንገተኛ የወሊድ መከላከያዎችን ጭምር በሁሉም ተንቀሳቃሽ የህክምና ቡድን ሥራዎች ውስጥ ማካተት፤ ተንቀሳቃሽ የህክምና ባለያዎችን በቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች ላይ ማሠልጠን እንዲሁም ቡድኖቹ ለውስጥ ተፈናቃዮች እና ለወጣቶች ተብለው የተዘጋጁ የመረጃ እና የትምህርት ቁሳቁሶችን እንዲያገኙ በማድረግ ያልተቋረጠ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መኖሩን ማረጋገጥ።

ለክልልመንግሥታት፣ ለወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች፣ ለጤና ተቋማት እና ለማኅበረሰብ ተኮር አወቃቀሮች

- ለጾታ ጥቃት ሰለባዎች የሚደረገውን የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መልሶ ማቋቋም ስራን ለመደገፍ ከተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎች እንዲሁም ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመተባበር እየተሰጡ ያሉ የገንዘብ ድጋፎች እና የሙያ ሥልጠና ፕሮግራሞችን ዘላቂነት ማጠናከር።
- ከአካባቢ ባለሥልጣናት ወይም ለሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢኮኖሚ መልሶ ማቋቋም ድጋፎች በሚደረጉበት ጊዘ የተጎጂዎች ምሥጢራዊ መረጃዎችን መጠበቅ ።
- ስለ ጾታዊ ጥቃት፣ በጤና ተቋማት ስለሚሰጡ አገልግሎቶች፣ ስለ ደኅንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ እንክብካቤ እና በቅርብ አጋር ስለሚፈጸም ጥቃት ግንዛቤ ለመፍጠር በአዋላጅ ባለሙያዎች መሪነት የሚደረጉ የማኅበረሰብ ውይይቶችን፣ የቤት ለቤት ጉብኝቶችን እና መደበኛ ያልሆኑ ስብሰባዎችን (ለምሳሌ የቡና ሥነ ሥርዓቶችን) መጠቀም።

- የጤና ተቋማትን አካላዊ ተደራሽነት (ለምሳሌ መግቢያዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ የምክክር ክፍሎች) በማሻሻል፣ ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ የሆኑ መረጃዎችን እና የመገናኛ ዘዴዎችን ማቅረብ እንዲሁም የጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች አክብሮት የተሞላበት እና ብቁ የሆነ እንክብካቤ እንዲሰጡ በማሠልጠን ለአካል ጉዳተኞች የጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽነትን ማሳደግ።
- ስለ ኤችአይቪ/ኤድስ ግንዛቤን ለመጨመር እና መገለልን ለመቀነስ እንደ ኤችአይቪ/ኤድስ ክለቦች፣ የሲቪክ ማኅበራት እና ማኅበረሰብ ውስጥ የሚሠሩ የማስተማር እንቅስቃሴዎችን መልሶ ማቋቋም።
- በቂ የነዳጅ አቅርቦት ለአምቡላንሶች እንዲኖር በማድረግ ሳምንቱን ሙሉ ያልተቆራረጠ የ24 ሰአት አገልግሎት መስጠት ፤ በዚህም የሪፈራል ሥርዓቱን ማጠናከር ።
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን፣ የውስጥ ተፈናቃይ ማህበረሰብ መሪዎችን፤ የአቻ አስተማሪዎችን እና የወጣት ክበቦችን በማሳተፍ ደኅንነቱ የተጠበቀ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ እና ከወሊድ በኋላ የሚሰጥ የወሊድ መከላከያን ጨምሮ ስለ ቤተሰብ ምጣኔ አማራጮች ግንዛቤን ማሳደግ እንዲሁም ለሴቶች እና ለወጣት ልጃገረዶች ስለ አገልግሎት አቅርቦት ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ማብቃት።
- መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከማኅበረሰብ ተኮር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተስማሚ የትምህርት ቁሳቁሶችን እና አገልግሎቶችን ማቅረብ ።
- በውስጥ ተፈናቃይ መጠለያ ካምፖች ውስጥ ለሚገኙ ታዳጊ ወንዶች እና ሴቶች በጤና ተቋማት ውስጥ የተለዩ እና ከዕድሜ ጋር ተስማሚ የሆኑ ቦታዎችን በመፍጠር ሁሉን አቀፍ የምክር አገልግሎት መስጠትን፣ የወሊድ መከላከያዎችን ማቅረብን እና እንደ ጾታዊ ጥቃት ያሉ ጉዳዮችን ሪፖርት ለማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ ስፍራ ማዘጋጀት ።
- ማኅበረሰቡ በጾታ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ዕቅድ እና ግምገማ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንደ የአስተያየት መስጫ ሣጥኖች፣ የማኅበረሰብ ስብሰባዎች እና የዳሰሳ ጥናቶች ባሉ መደበኛ እና የተዋቀሩ የአስተያየት መስጫ ዘዴዎች በማዘጋጀት የማኅበረሰብ ተሳትፎን ማጠናከር።

ለክልል ጤና ቢሮዎች፣ ለክልል የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶች ወይም ለሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ

- ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት የአካባቢ ጤና ተቋማትን በሠለጠነ የሰው ኃይል እና በቂ ግብአቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ፤ ይህ እንዲሳካ ለማድረግም በተለይም በአማራ ክልል በክልሉ መንግስት፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በጤና ተቋማት መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር።
- ከኤችአይቪ ጋር በተያያዘ መገለልን እና የተሳሳተ መረጃ ስርጭትን ለመቅረፍ ለጤና ባለሙያዎች ኤችአይቪ ላለባቸው እናቶች እና ኤችአይቪን ለመከላከል የሚደረግ የቅድመ-ተጋላጭነት ሕክምና ላይ በዓለም ጤና ድርጅት የተዘጋጀውን መመሪያን መሰረት በማድረግ የሥልጠና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት ።
- በተለይም የውስጥ ተፈናቃዮች ባሉባቸው ጣቢያዎች ወስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦችን ፤ ቁልፍ የሕዝብ ክፍሎችን እና በርካታ የወሲብ አጋሮች ያሏቸውን ሴቶች እና በወሲብ የሚተዳደሩ ሰዎችን ከኤችአይቪ/የአባለዘር በሽታዎች ለመከላከል የግንዛበ ማስጨበጫ ትምህርቶች እና የማኅበረሰብ ተደራሽነት ፕሮግራሞችን ማጠናከር።
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን የአገር አቀፍ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ ደህንነቱ እና ሚስጥራዊነቱ ከተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ጋር ማቀናጀት ፤ ከአግልዎ ነጻ በሆነ መልኩ ባለሙያዎች ከፅንስ ማቋረጥ በኋላ የቤተሰብ ምጣኔ ምክር እና አገልግሎትን ለተገልጋዮች እንዲሰጡ ማሠልጠን እንዲሁም አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ የህክምና ቁሳቁሶች በመሰረታዊ የህክምና ግብአት ዝርዝሮች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ ።
- የሥነ-ተዋልዶ ጤና መሣሪዎች የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ የአቅርቦት ሰንሰለት መዘግየቶችን መቀነስ እና ተቋማት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን (ለምሳሌ ኮንዶም፣ የአባለዘር በሽታዎች ሕክምና መስጫ ዕቃዎች፣ ንጹሕ የማዋለጃ ቁሳቁሶች፣ አስፈላጊ የጨቅላ ሕፃናት መሣሪያዎች፣ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብአቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ እና ሲያልቁ በጊዜው የማሟላት ሥራን መተግበር ። ከዚህ በተጨማሪም የወርኃዊ ክምችት ሁኔታን ዳሽቦርዶችን ወይም ለሎች ተንቀሳቃሽ ሪፖርት ማድረጊያ መሣሪያዎች በመጠቀም መከታተል ።

የመጨረሻ ማስታወሻዎች

1. MOH. 2021. Ethiopia Reproductive Health Strategic Plan (2021-2025).
2. Ethiopia: Internal Displacement Overview (as of June 2024) | OCHA (unocha.org)
3. IOM. 2022. Ethiopia - data for sustainable support to persons displaced by conflict and natural disasters and their host communities, household level survey (HHs), Amhara region (march 2024): IDPS, returning IDPs and non-displaced residents.
4. Ethiopia - Situation Report, 1 Mar 2024 | OCHA
5. Ethiopia: Floods - May 2024 | ReliefWeb
6. Ethiopia: Internal Displacement Overview (as of June 2024) | OCHA
7. Fisseha G, Gebrehiwot TG, Gebremichael MW, et al. War-related sexual and gender-based violence in Tigray, Northern Ethiopia: a communitybased study. BMJ Glob Health 2023;8:e010270. doi:10.1136/ bmjgh-2022-010270.
8. ETHIOPIA Protection Analysis Update: Update on conflict and climate-related protection risks trends
9. Gebregziabher M, Amdeselassie F, Esayas R, et al. Geographical distribution of the health crisis of war in the Tigray region of Ethiopia. BMJ Global Health 2022;7:e008475. doi:10.1136/bmjgh-2022-008475
10. Arage, MW, et al. 2022. Assessing the health consequences of northern Ethiopian armed conflict, 2022. Journal of Public Health Policy (2024) 45:43–57
11. Tsadik, M. et al. 2024. Neonatal mortality during the war in Tigray: a cross-sectional community-based study. Lancet Glob Health 2024; 12: e868–74. Neonatal mortality during the war in Tigray: a cross-sectional community-based study
12. Tadesse A, et al. 2024. Quality of neonatal health care in comprehensive specialized hospitals, Amhara Region, Ethiopia: a retrospective study with neonatal death audit. BMC Health Services Research (2024) 24:1173, 12913_2024_Article_11681.pdf

HEALTH
CLUSTER

HEALTHCLUSTER.WHO.INT